09/08/2010ዓ/ም

# በፃዕዳ ርእሰማልነት ግንባታ ማእቀፍ ውስጥ የሰራተኞች ተሳትፎና ተጠቃሚነት በኢትዮጵያ

## 1.መግቢያ

ኢትዮጵያ ፃዕዳ ርእሰማልነት(Capitalism) እየገነባች ነው።ይህ በመገንባት ላይ ያለ ስርዓት በተረጋጋ መንገድ ሲጓዝ ቆይተዋል።ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የመንገራገጭ ሁኔታ እያጋጠመው ነው።ስርዓቱ ያጋጠመው ግዝያዊ አለመረጋጋት ተከትሎ ዜጎች የችግሩን መንስኤና መፍትሄ የሚሉትን ገንቢ ሓሳብ በማቅረብ ላይ ናቸው።ይህ ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።ሙሁራን ጥናት በማጥናት የችግሩ መንስኤና መፍትሄ ለመንግስትና ለህዝብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።ይህ የሙሁራኑ ጥናትና ምርምር በአሁኑ ሁኔታ ቢቻ ተገድቦ መቅረት የለበትም።በቀጣይነት መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው።የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ስርዓቱ ካጋጠመው መንገራገጭ ለማውጣትና ቀጣይነት ያለው ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ በስርዓቱ ማዕቀፍ ውስጥ በመሆን ሰራተኞች መከተል ያለባቸው የትግል አቅጣጫ ለማመላከት ያለመ ነው።

## 2.የኢትዮጵያ ሰራተኞች ትግል ታሪካዊ አመጣጥ

በኢትዮጵያ ጥገኛ ርእሰማልነት ማቆጥቆጥ ከጀመረበት ግዜ አንስቶ የባለሃብትና ሰራተኛ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል።እንደሚታወቀው ከ1946 በፈረንጆች አቆጣጣር ጀምሮ የተባበሩት መንግስታት አካል ሆኖ በመስራት ያለውን ዓለም ዓቀፍ የሰራተኞች ድርጅት (ILO) ሰራተኛና አሰሪ በነፃነት የመደራጀት መብት እንዳላቸው መደንገጉን ይታወቃል።ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ሰራተኞች በዘውዳዊውና ጥገኛ ርእሰማልነት በነፃነት የመደራጀት መብታቸው ተነፍጓቸው ቆይተዋል።በስርዓቱ ለሚደርሳቸው በደል ለመመከት በተለያየ ግዜ የተለያየ የትግል ስልት ተከትለው ታግሏል።በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የመደራጀትን አስፈላጊነት በመረዳት ለመደራጀት ትግል ያደረገና  የተታገለ የሰራተኛው መደብ የሚቀድመው አልነበረም።የኢትዮጵያ ሰራተኞች በድብቅ የመረዳዳት ማህበር በመመስረት ጀምረው ህጋዊ እውቅና ያለው ማህበር እንዲሸጋገር ባካሄዱት ትግል  ዘውዳዊውና ጥገኛ ርእሰማልነት ስርትዓት ሳይወድ በግድ የሰራተኛው ማህበር ለማደረጀት የሚፈቅድ አዋጅ እንዲያወጣ በማስገደድ የኢትዮጵያ ሰራቶኞች በአገር ዓቀፍ ደረጃ የሰራቶኞች ማህበር አደራጅቷል።የሰራተኞች መደራጀት ለስርዓቱ ስጋት ስለሆነው የሰራተኛ ማህበር መሪዎች በስርዓቱ የዓፈና መዋቅር ወደ ማሰርና መግደል ተሸጋገረ።ሰራቶኞች ይህንን ያህል ግፍ እየደረሰባቸው ትግላቸውን የሚያቆመው አካል ግን አልነበረም።የትግራይ ቀዳማይ ወያኔ፣ የባሌ/ኦሮሞና የጎጃም አርሶደሮች ዓመፅ ተዳምሮ ስርዓቱ እንዲንገዳገድ አደረገው።

መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ከጫፍ ጫፍ በአከሄዱት ዓመፅ ምክንያት በ1966ዓ/ም የፈነዳው የኢትዮጵያ አብዮት ዘውዳዊው ስርዓት ከዙፋኑ እንዲገረሰሰ አደረገው ።በተካሄደው ህዝባዊ ዓመፅ ሰራቶኞች ስራ የማቆም አድማ በመጥራት ወደ ህዝባዊ ዓመፁ በመቀላቀላቸው ስርዓቱ በፍጥነት እንዲሽመደመድ እንደአደረገው ብዙዎች ፖለቲካ ተንተኞች ይስማማሉ።

መሬት ላራሹ፣የብሄር ብሄረሰብና የሴቶች እኩልነት እንዲከበር፣ስልጣን የህዝብ እንዲሆን መፈክር አንግቦ ያመፀ ህዝብ ግን የስልጣን ባለቤት መሆን አልቻለም።በአንፃሩ ወታደራዊ ደርግ ስልጣኑን ተቆጣጥሮ ጥገኛ ርእሰማልነት በፋሽስት መንገድ በማስቀጠል  ሰብአዊና ዲሞክራስያዊ መብቶች በኣዋጅ  ቢያግድም  የሰራቶኞች ትግል ግን አልቆመም።

ደርግ የህዝቡን ዓመፅ በመጨፍለቅ ወደ ስልጣን ከወጣ ጊዜ ጀምሮ የሓይሎች አሰላለፍ ለውጥ መታየት ጀመረ።የሰራተኛ ጥቅም ማረጋገጥ የሚቻለው በየትኛው መንገድ ነው በሚል ጥያቄ ላይ ልዩነት ተፈጠረ።

በዚህ አሰላለፍ እንደ አንድ የሃይል አሰላለፍ የሚታየው በስልጣን የነበረው ደርግ ነው።ይህ ሃይል በህዝቦች ትግል ወደ ስልጣን የመጣ ሃይል አይደለም።የነበረውን ጥገኛ ርእሰማልነት በፋሽስት መንገድ መልኩን በመቀየር ስልጣኑን ለማስቀጠል ወደ ስልጣን የወጣ ሓይል ነው፤ይሁን እንጂ በወቅቱ የነበረው በአገር ውስጥ የተፈጠረው አብዮታዊ ንቅናቄ ተራማጅ ብትሆንም ባትሆንም የተራማጅ መፈክር እንድትይዝ የሚያስገድድ ወቅት በመኖሩ ምክንያት ደርግም የርእሰ-ዴሳዊ( Communist ) ሪኦት እከተላሎሀ እንዲል አስገደደው።በስመ ዴስነት(socialism) የሚነግድ የሰራቶኞች ፓርቲ /ኢሰፓ/እስከ መመስረት ደረሰ።የሰራቶኞች ጥቅም ለማስከበር በሚል ሽፍጥ ዜጎች በጥረታቸው

ያፈሩትን ሃብት እስከመውረስ ደረሰ።በስመ ዴስነት(socialism) መንግስታዊ ጥገኛ ርእሰማልነት እንዲጠናከር አደረገ።

ሌላው የሃይል አሰላለፍ በኢህአፓ መወከል የሚችል አሰላፍ ነው።ኢህአፓ ጥቁር ቦልሸቪክ ነኝ (ቦልሾቪክ፤በሶቭየት ሕብረት የሰርቶ አደሮች ፓርቲ ነው) ብሎ ራሱን በመጥራት በኢትዮጵያ አንጋፋ የሰራተኞች ፓርቲ አድርጎ በማሰብ የሚንቀሰቀስ ፖለቲካዊ ድርጅት ነው።ኢህአፓ የብሄር ጥያቄ መደባዊ ትግል ይገድላል በሚል ሰበብ የብሄር ጥያቄ ወደጎን በመተው፣አርሳአደሩም መሬት በደርግ ስለ ተከፋፈለ የገጠር የትጥቅ ትግል ሊሸከም አይችልም በሚል ምክንያት የከተማ ዓመፅ በአቋራጭ ስልጣን የሚገኝበት መንገድ መስሎ ስለ ታየው የከተማ ዓመፅን ማቀጣጠሉን ተያያዘው።በዚህ የተሳሳተ የትግል መንገድ ብዙ ሙሁራን ወጣቶች እንዲሁም እስከ ፋብሪካዎች በመዝለቅ ሰራቶኞች ከጎኑ ለማሰለፍ ተንቀሳቀሰ።በዚህ እንቅስቃሴው ቀላል የማይባል ድጋፍም አግኝቶ ነበር።ከፍተኛ የደርግ ባለ ስልጣናትም እስከ የመግደል ሙካራ አካሄደ።ውጤቱ ግን የታሰበው ሊሆን አልቻለም።ይህ የተሳሳተ የትግል አቅጣጫ ኢትዮጵያ ያፈራቻቸው ወጣት ሙሁራንና ሰራቶኞች የጥይት ሲሳይ ሆኑ።በትግራይ የሚንቃቀስ የነበረ ኢህአሰ /የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት /በኢህአፓ የተዋቀረው ሰራዊትም በአመራር ችግርና በውስጡ በተፈጠረው ቅራኔ ለውድቀት ተዳረገ።በመጨራሻም በህወሓት ላይ ጦርነት አወጀ።ህወሓት ራሱን ለመከላከል ባካሄደው ውግያ ኢህአፓ ከትግራይ መሬት ተጠራርጎ ወጣ።ጥቁሩ ቦልሸቪክ ኢህአፓ ቀደም ሲል በተገለፀው መንገድ ተበታትኖ ቀረ።

ከላይ ከተጠቀሱት አሰላለፎች በመሰረቱ የተለየ አሰላለፍ ይዞ የመጣ በህወሓት/ኢህአዴግ የሚወከል የጭቁን ህዝቦች አሰላለፍ ነው።በመጨራሻም ወደድል የበቃው ይህኛው አሳላለፍ ነው።

ህወሓት/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ የማታገያ መፈክር የብሄር ጥያቄ መሆኑንና በብሄራዊ ጥያቄ በማናሳሳት፣ በማደረጀትና በማታገል ወደ መደባዊ ንቃት እንዲሸጋገርና መደባዊ ጥቅሙን ማስጠበቅ ይቻላል በሚል እምነት ብሄራዊ አደረጃጀት በመከተል የተራዘመ የገጠር ትግል ለማካሄድ የካቲት 11 /1967 ዓ/ም ደደቢት በረሃ የትግሉን ችቦ ሎኮሰ።

ኢህአዴግ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፕሮግራም ስለሚመራ አብዮታዊ ሙሁር፣አርሶአደር /አርብቶኣደር፣ሰርቶአደሮችና የከተማ ነዋሪዎች ከጎኑ በማሰለፍ፤ መስፍንነት(Feudalism)፣ ጥገኛ ርእሰማልነት ከስር መሰራታቸው ነቅሎ ለመጣል የተታገለ ድርጅት ነው።ኢህአዴግ ብዙሃን ህዝብ ለድል መብቃት የሚችለው በተደራጀ መንገድ ነው በሚል ፅኑ እምነት በማህበር፣ በህዝባዊ ባይቶ /ህዝባዊ ሸንጎ ደረጃ በማደራጀት ታግሎ ያታገለ ድርጅት ነው።በህወሓት/ኢህአዴግ ከተደራጁት ማህበራት የሰራቶኞች ማህበር አንዱ ነው።ይህ ማህበር ለመጀመርያ ግዜ የተደራጀው በትግራይ ሽራሮ ከተማ መሆኑን ይነገራል።አንድ አንዶቹ ይህ የሰራቶኞች ማህበር ለመጀመርያ ጊዜ ከማንኛውም ህወሓት ካደራጃቸው ማህበራት ቀድሞ የተደራጀ ማህበር ነው ብለው ሲከራከሩ፤ አይደለም በህወሓት ከተደራጁት ማህበራት ቀድሞ የተደራጀው የሴቶች ማህበር ነው፤ የሰራታኞች ማህበር የሴቶች ማህበር ተከትሎ ነው የተዳረጀው ብለው የሚከራከሩ ስላሉ በጥናት መመለስ ያለበት ጉዳይ ነው።ይሁንጂ የሰራተኞች ማህበር ቀድመው ከተደራጁት ማህበራት አንዱ መሆኑን ግን የሚያከራክር አይደለም።ይህ ሃቅ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ህወሓት/ኢህአዴግ በመጀመያው የትግል ዓመታት የሰራተኞች ማህበር ተደራጅቶ እንዲታገል ያደረገበት ምክንያት በኢትዮጵያ ሰራቶኞች እንዳማንኛውም ህዝብ በቢሄራዊ ማንነታቸው በደል ሲደርስባቸው የነበረ መሆኑ፣ ከዚህ በተጨማሪም ጉልበታቸው በከፍተኛ ደረጃ የሚመዘበሩ መሆናቸው በአብዮታዊ ዲሞክራስያዊ መስመር በማታገል ተጠቃሚ ማድረግ ስለሚቻል የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ታማኝ ሃይል መሆናቸውን በፅናት ስለተማነበት ነው።

በዚህ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መስመር እየተመራ ትግሉን ያጠናከረ ኢህአዴግ ቁጥራቸው የማይናቁ ሰርቶአደሮች በትጥቅ ትግሉ ወቅት አታግለዋል በፅናት ታግለዉም መስዋእት ሁኖዋል።

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የትግራይ ሰርቶአደሮች በማደራጀትና በማታገል ብቻ ሳይታጠር የመሃል አገር ሰራተኞች ለትግል እንዲነሳሱ ሰፊ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ስራ ሰርተዋል።በስመ ሰርቶአደር የሚነግድ ደርግ ለሰርቶአደሩ እንዳልቆመና በሰርቶአደር ትግል ስርዓቱ መፍራስ እንዳለበት በምትኩ ሰርቶአደር ከብዙሃኑ ህዝብ ጋር ተጠቃሚ የሚሆንበት ስርዓት መገንባት እንዳለበት በሰፊው ቀስቅሰዋል አስተምሮዋል።በኢህአዴግ በተሰራ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ስራ ሰርቶአደሮች ከኢህአዴግ ጎን ተሰልፈው ታግላዋል።ደርግ ለመገርሰስ የተደረገ መራራ ትግል ከብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝቦች ውስጥ ሰርቶአደሮች የበኩለቸውን ሚና ተጫውቶዋል።

ይህንን ያህል የተታገለ የሰራተኞች መደብ በኢትዮጵያ በመገንባት ካለው ርእሰማልነት ምንያህል ተጠቃሚ መሆን እንደቻለ ወደ የሚያሰየን ይዘት እንሸጋገር።

## 3. ሰራተኛው በመገንባት ላይ ካለው ርስማልነት ምን ጥቅም አገኘ?

ሰራተኛ ዋናው የሚፈልገው ነገር ቢኖር ሰላም ነው።ሰላም ለሰራተኛው ህዝብ ከማንኛውም በላይ ነው።በኢትዮጵያ በመገንባት ላይ ያለው ርእሰማልነት ሰራተኛው ሰላም እንዲገኝ በማድረጉ ከሰላሙ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሎታል።በዚህ አገር ሰላም በመኖሩ የማንኛውም ብሄር ብሄረሰብ ተወላጅ በፈለገው የኢትጵያ መሬት ተንቀሳቅሶ የመስራት ዕድል ፈጥሮለታል።ያገኛትን ገቢ ቆጥቦ ኑሮውን ለማሻሻል እንዲያውላት ሰላም የማይተካ ሚና ተጫውቷል።ሰላም በመኖሩ ምክንያት ብዙ ሰራቶኞች ኑሮቸው ተሻሽለዋል።

የኢትዮጵያ ርእሰማልነት ለልማት ቅድሚያ የሚሰጥ ከልማቱም ብዙሃኑ ህዝብ በየደራጀው ተጠቀሚ የሚያደርግ ስርዓት ነው።ከዚህ በተጨማሪም የተመረጠና የተቀናጀ የመንግስት ጣልቃገብነት የሚከተል የነፃ ገበያ ስርዓት ነው።ማንኛውም የሰው ጉልበት ሳትባክን ለማሳማራትና ከስምሪቱም ከሚገኘውን ዕድገት ብዙሃኑ ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚንቀሳቀስ የገባያ ስርዓት ነው።

በዚህ የገበያ ስርዓት ፈጣን እድገት ለማስመዝገብ ችለዋል።ከዚህ ፈጣን እድገት ሰራቶኞች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል ።ሰራቶኞች በየጊዜው ኑሮአቸው እየተሻሻለ መጥተዋል። የትምህርት የጤና አገልግሎት ማግኘት ችለዋል።ከቀደምት ሰራተኞች የሚለዩበት ከመሰረተ ትምህርት እስከ ከፍተኛ ትምርት የደረሱ መሆናቸው ጉልበታቸውና ሞያቸው/ እውቀታቸው/ አጣምረው ስራ ላይ የሚያውሉ ሰራቶኞች በብዛት እየተፈጠሩ መምጣታቸው የፈጣን እድገት ውጤት ነው።

በኢትዮጵያ እየተመዘገበ ያለው ፈጣን እደገት ብዙ ስራአጥ ወጣት ስራ እንድያገኝ እድል ፈጥረዋል።በኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ገቢ ማሻሻል አሳይተዋል ሲባል የሰራተኛው ገቢም ጭምር መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ ነው።

የመንገድ፣የተሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ወዘተ /ከመሰረተ ልማት/ ሰርቶ አደሩ ተጣቃሚ ለመሆን ችለዋል።የትኛው አከባቢ ምን ዓይነት የስራ እድል እንዳለ በእጁ በያዛት ሞባይል መረጃ የሚያገኝበት ሁኔታ ፈጥሮለታል።ስራ ወደአለበት ቦታ በፍጥነት የሚያደርስ መንገድ በመሰራቱ ፈጥኖ ለመድረስ አግዞታል።

ከላይ በተጠቀሱት ለውጦች ምክንያት በኢትዮጵያ አማካይ የሰው ልጅ የመኖር እድሜ 64 ዓመት ደርሶዋል ሲባል የሰራተኛው የመኖር እድሜም ያካተተ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል።

ሌላው የሰራቶኞች ተጣቃሚነት አረጋግጠዋል ከሚባሉት አንዱ የዲሞክራሲ መስፈን ነው።የዲሞክራሲ መስፈን ዋናው ምሶሶው ህገመንግስት ነው።ሕገ መንግስት ማንኛውም ዜጋ በፈለገው ቦታ ተንቀሳቅሶ የመኖር ፣ሰርቶ የመክበር መብት እንዲጎናፀፍ አስችለዋል።ሕገ መንግስት ሰራተኞች በማህበር የመዳረጀት፣ከአሰሪያቸው የመዳራደር መብት እንዲጎናፀፉ አስችለዋል።ህገ መንግስት የሰጣቸውን መብት በመጠቀም ጥቅማቸውን የማስጠበቅ እንቅስቃሴ እያደረጉም ይገኛሉ።ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮያ ካለው ህጋዊ ፖለቲካዊ ድርጅት በአባልነት ተመዝግቦው በነፃ ሐሳባቸውን የሚያራምዱበት እድልም ተፈጥረዋል።

ሰራቶኞች በርእሰማልነት ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ሊከበርላቸው የሚችለውን ሁሉን መሰረታዊ መብቶች በሕግ ተከብሮላቸዋል።የዚህ መብት በሕግ መከበሩ አንድ ጉዳይ ሁኖ በዝቅተኛ፣መሃከለኛና ከፍተኛ ደረጃ የመጠቀም ጉዳይ ግን የሰራተኛው የመዳረጀት፣የማህበሩ ጥንካሬ እንዲሁም የተሰለፈበት ፖለቲካዊ አሰላለፍ ይወስነዋል።ጠንካራ አደረጃጀት ከተፈጠረ በከፍተኛ ደረጃ በዓለም ገበያ ሕግጋት መሰረት የመደራደር ዓቅሙን ይጨምራል።ደካማ አደረጃጀት ካለው ደግሞ በዓለም የገበያ ሕግጋት መሰረት የመደራደር ዓቅሙ ይዳከማል ማለት ነው።

ስርዓቱ ሰራተኛው የሚጠቀምበት ዕድል የፈጠረና በተግባርም እየተጠቀመ ያለ ቢሆንም፣ ሰራተኛው መጠቀም ያለበት ደረጃ እየተጠቀመ ነው ለማለት ግን አያስደፍርም። ሰራተኛው እንዲሟሉለት የሚፈልጋቸው ጥቅሞች ምን ምን ናቸው የሚለውን ቀጥለን እንመለከት።

## 4.ሰራቶኞች እንዲሟሉለላቸው የሚፈልጉዋቸው ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

ሰራተኞች ቀጣይነት ያለው የተረጋጋ ሰላም እንዲኖር ይፈልጋሉ።ከቅርብ ግዜ ወዲህ በአገራችን እየታየ ያለውን ጊዚያዊ አለመራጋጋት ተከትሎ ሰራቶኞች ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም እንዳያገኙ እያደረገ ነው።ሰራተኞች በብሄራዊ

ማንነታቸው ጥቃት እየደረሳቸው ነው።ሰርተው ያፈሩትን ሃብት የውጭና የውስጥ የቀኝ አክራሪ ሃይሎች በፈጠሩት ብጥብጥ እየወደመ ነው።ተቀጥረው የሚሰሩባቸው ፈብሪካዎች በቀለም አብዮት አቀንቃኞች በፈጠሩት ሁውከት የሚቃጠሉበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።ፈጥኖው ወደ ስራ እንዳይሄዱ በነውጠኞች መንገድ የሚዘጋበት ሁኔታ ስላለ የሚቸገሩበት ሁኔታ እየታየ ነው።ይህ ሁኔታ ሰራተኞች ማግኘት የሚገባቸው ጥቅም እንዳያገኙ እያደረገ ነው።

ፈጣን ልማት ለሚፈጠረው ወጣት ስራእድል እንዲያገኝ በስራ የተሰማራውን ሃይልም ኑሮውን እንዲሻሻል ዕድል ይፈጥራል።ለሚፈጠረው ስራ ፈላጊ ወጣትና ኑሮው ለማሻሻል ለሚፈልግ ሰራተኛ መልስ የሚሰጥ ፈጣን እድገት ማስመዝገብ ይጠይቃል።ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ ስንመለከት ልማቱና ከልማቱ ተጠቃሚነት መመጣጠን አልቻለም። ኢትዮጵያ ባስመዘገበችው ፈጣን እድገት ብዙ የተማረ የሰው ሃይል መፍጠር ችላለች።ይሁን እንጂ ሁሉንም የተማረ በሞያውና ችሎታው ወደ ስራ ሊሰማራ አልቻለም።ይህ ሁኔታ የበይ ተመልካች በብዛት እንዲፈጠር ምክንያት ሁኖዋል።ይህ የበይ ተመልካች ውሱን ገንዘብ በመርጨት የፖለቲካ ዓላማቸው ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ የውስጥና የውጭ ቀኝ አክራሪ ሃይሎት የተመቻቸ ሁኔታን ፈጥሮላቿል።

ከዚህ በተጨማሪም በስራ ላይ ያለው ሰራተኛም ቢሆን ከእድገቱ ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ተጠቃሚ መሆን አልቻለም።በግልም ይሁን በመንግስት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሃይል የኑሮ ውድነት እያንገዳገደው ይገኛል።ኢቢሲ በዜና እወጃው እንደአቀረበው ኮሆነ በኢትዮጵያ ጥሩ ገቢ አላቸው ከሚባሉት ባለ ሃብትና በአማካሪነት የተሰማሩ ከፍተኛ ሙሁራን መሆናቸውም ገልፀዋል።አብዛኛውን በደመወዝ የሚተዳደር ሰራተኛው ክፍል ግን በኑሮ ውድነት እየተቸገረ እንዳለ ገልፃዋል።

ለእኩል  ስራ እኩል ደመወዝ እንዲከፈል ሕግ የሚፈቅድ መሆኑን ቢታወቅም ሴቶች ሰራተኞች ከወንዶች እኩያቸው እኩል ክፍያ የማይከፈልባቸው ሁኔታም በግልፅ እየተያ ነው።

ዲሞክራሲ ለሰራተኛው ጥቅም መከበር ሁነኛ መሳርያ ነው።ዲሞክራሲ ሲጠፋ የሰራተኛው ጥቅም አብሮ ይጠፋል።የሰራተኛው ጥቅም የሚያስጠብቅለት ማህበር እንዳይኖሮው የተለያየ ጫና እየተፈጠረበት ነው።ኢቢሲ በዜና እወጃው እንዳስነበበው በአምራች ዘርፍ የተሰማሩ ሰራተኞች 2.5 ሚልዮን የሚደርሱ መሆናቸውን ገልፆ በማህበር የመደራጀት እድል ያገኙት ከ10% እንደማይበልጡ አስነብበዋል።እነዚህ የመደራጀት እድል ያገኙት ከመንግስት ፕሮጀችቶችና እንደነ ትእምት/EFFORT/የመሳሰሉ የህዝብ ተቋማት ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም።

ይህ ብቻ አይደለም የኢትዮጵያ ሰራቶኞች ችግር።በስራ ቦታቸው ለጥንቃቄ የሚያስፈልጉ መሳርያዎች የማይቀርቡለት ሁኔታም በኢትዮጵያ በስፋት እየታየ ነው።ለጥንቃቄ የሚያስፈልጉ መሳርያዎች የማይቀርብለትና ባለ መቅረቡ ለአካል ጉዳተኝነት የሚጋለጥ ሰራተኛ ቁጥሩ እየጨመረ ነው።ከዚህ በተጨማሪም ለሚደርሰው የአካል መጉደል ተገቢ ካሳ ሳይከፈለው ከስራ የሚሰናበት ሰራተኛ ቤቱ ይቅጠረው።ይህንን የመሰለ ችግር እንዳለ ፋና ብሮድካስትንግ ኮርፖሬት ራድዮ በሚያስተላልፈው ፕሮግራሙ ያቀረበበት ሁኔታ መኖሩን የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።የኢትዮጵያ አሰሪና ሰራተኛ ህግ ምን እንደሚል ሰራተኞች እያጋጥማቸው ያለ ችግር በህግ አንፃር እንዴት መታየት እንዳለበት በማብራራት ዘግቦታል።

እስኪ በመጨረሻ ሰራተኞች የተፈቀደ የጡሮታ አበል አተገባበር እንመልከት።ከመንግስት መስራቤት ውጭ / በግል/ተቀጣሪ ለሆኑት ሰራተኞች የጡረታ አበላቸው አተገባበር እንዲከታተል የተቋቋመው ኤጀንሲ በአንድ ወቅት ለፋና ብሮድካስትንግ ኮርፖሬት እንደገለፀው ከተወሰኑ ባለሃብቶች በስተቀር ሌሎች የግል ተቋማት ሊተገብሩት እንዳልቻሉ በመግለፅ አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስድ ያስጠነቀቀበት ወቅት እንደነበርም የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው።

ከላይ የተገለፁት ጉዳዮች በመመልከት የኢትዮጵያ ሰራቶኞች በርእሰማልነት ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ  ጥቅማቸው ለማረጋገጥ ብዙ ትግል እንደሚያስፈልጋቸው የሚያንፀባርቅ ነው።ከዚህ በመቀጠል የኢትዮጵያ ሰራተኞች በርእሰማልነት ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ወይም ዓለም ዓቀፍ የገበያ ሕግጋት ተግባራዊ በማድረግ ጥቅማቸው ለማስከበር መከተል ያለባቸው የትግል አቅጣጫ ምን መምሰል እንዳለበት ወደምናይበት ቀጣዩ ይዘት እንሸጋጋር።

### 5.**የኢትዮጵያ ሰራቶኞች ተባበሩ።የኢህኣዴግ ሰልፍ አጠናክሩ።**

የኢትዮጵያ ሰረቶኞች ያገኟቸውን ጥቅሞች በቀጣይነት ለማስጠበቅ የቀራቸውን ጥቅሞች ለማግኘት ጠንክረው መታገል ይገባቸዋል።ለመነሻም የሚከተሉት አቅጣጫዎች ለማስቀመጥ ተመኩሯል።

## 5.1.የኢትዮጵያ ሰራተኞች ተባበሩ!

ቀደምት የኢትዮጵያ ሰራተኞች መብታቸው ለማስከበር ሁሉንም መብቶች አፍኖ የያዘው ስርዓት ውስጥ ሆነው ማሕበራቸው በድብቅ አደራጅተው፣ቀጥለውም በሕጋውነት ማህበር እንዲደራጁ በኢፋ ጠይቀው በሕጋዊ መንገድም ማሕበር መስርተው ለጥቅማቸው ሰፊ ትግል አድርገው መተኪያ የለላትን ሂወታቸው ከፍለዋል።

በኢህአደግ የሚመራ ትግል ከተጀመረ በኋላም ከኢህአዴግ ሰራዊት ጎን ተሰልፈው ኩቡር ሂወታቸውን ሰውተዋል።

የአሁኑ ሰራተኛ የሰማእታት ፈለግ ተከትሎ መታገል አለበት።ሰራተኛ የቀኝ አክራሪዎች ያዘጋጁትን ወጥመድ ለመበጣጠስ መተባበር አለበት።የሰራተኛ መለያ ባህሪው በዘር በሃይማኖት በብሄር አይከፋፈልም።ሰራተኛ ዓለም ዓቀፋዊ ባህሪና ይዘት ያለው መደብ ነው።በመከፋፈል ሳይሆን በመተባበር አንድ በመሆን ነው ጥቅሙን ማስጠበቅ የሚቻለው።አንድ ሁኖ ለመታገል ወሳኝ ምክንያት ችግሩንም ጥቅሙንም መፍትሄውም አንድ ስለሆነ ነው።ትግራዋይ፣አማራ፣ኦሮሞ፣ደቡብ ህዝቦች ወዘተ ያለው ሰራተኛ ሰላም አጥብቆ ይሻል፣ስራ እድል እንዲፈጠርለት ይፈልጋል፣ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ መስራት ይፈልጋል የስራ ዋስትና እንዲኖሮው ይፋልጋል፣ንሮው እንዲሻሻል ወዘተ እነዚህ ጉዳዮች እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ሰራተኞች በዓለም ላይ ላሉት የማንኛውም አገር ሰራተኞች ፍላጎት ናቸው።በዚህ ምክንያት ነው የኢትዮጵያ ሰራተኞች በርእሰማልነት ውስጥ ያለው አንድ ወሳኝ መደብ መሆናቹሁ በመገንዘብ መተባበር ያለባቹሁ።

## 5.2.የኢትዮጵያ ሰራተኞች ጠንካራ አደራጃጀት ይኑሯቹሁ

ጠንካራ አደራጃጀት በሌበት ከፍተኛ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አይቻልም።በዚህ ምክንያት ጠንካራ አደራጃጀት እንዲኖሯቹሁ መታገል ይገባል።

ማጠንከር ካለባቹሁ አደራጃጀታቹሁ አንዱ የሰራተኛው ማህበራት ነው።የሰራተኛው ብቃት ከጊዜ ጊዜ እንዲሻሻል ከአሰሪው ጋር ጠንክሮ ለመደራደር ዘላቂ የኢንዳስተሪ ሰላም እንዲረጋገጥ ጠንካራ የሰራተኛ ማህበራት ይጠይቃል።ስለዚህ የሰራተኛ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ መታጋል ይገባል።

ሌላው አደራጃጀት የፖለቲካዊ ፓርቲ አደራጃጀትን የተመለከተ ነው።ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም አደራጃጀት ሕግን ተከተሎ የመደራጀት መብት አለው።ሰራተኛም የራሱ የሰራተኞች ፓርቲ የመመስረት መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።ይህ የሰራተኞች ፓርቲ የማደረጃት ጉዳይ የራሱን ጊዜ ይጠይቅ ይሆናል።በቅርብ ርቀት ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው የሰራተኛው መብት ለማስጠበቅ የሚያስችል ዓቅምና ብቃት ያለው ኢህአዴግ ድርጅታቹሁ ማጠናከር እንደ አቅጣጫ መከተል ተገቢ ነው።ሰራተኛ በብዛት ወደ ኢህአዴግ አባል ድርጅቶች (ህወሓት፣ብአዴን፣ኦህዴድ፣ ደኢህዴን) በብዛት አባል ሁኖ መግባት ይገባል።ይህ አካሄድ በኢህአዴግ ውስጥ ለሰራተኛ ጥቅም መረጋገጥ እቅድ ሲያዝም ሲተገበርም በንቃት በመሳተፍ ለተፈፃሚነቱ ለመረባረብ ዕድል ያገኛል።ከዚህ በተጨማሪም ሰራተኛ በሚያደርገው ንቁ ተሳትፎና ብቃቱ እየታየ ወደ አመራርነት እንዲመጣ እድል ያገኛል።ስለዚህ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ኢህኣዴግ የማጠናከር አቅጣጫ ተከትለው ትግላቸው ማጠናከር ይገባል።

## 5.3.ሰራቶኞች ለልማታዊ ባለሃብት መደገፍና ማበረታት አለባቹሁ

ሰራተኞች በርእሰማልነት ስርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ማግኘት የሚቻለው ልማታዊ ባለሃብት በቁጥር፣በአቅምና በአደረጃጀት ሲጠናከር ነው።ከልማታዊ ባለሃብት ዓለም ዓቀፍ የገበያ ሕግጋትን በመከተል እንዲደራደር አቅም ይኖረዋል።ልማታዊ ባለሃብት ለሕገ-መንግስቱ ተገዥ ስለሚሆን ሰራተኞች በመደራጀታቸው ስጋት አይሰማውም።የሰራተኞች ማህበር በእያንዳንዱ ሰረተኛ ከመደራደር ከማህበሩ መደራደር ጊዜና ወጪው ስለሚቀንስለት ተመራጭ መንገድ መሆኑን ያምናል።እንዲዚህ ዓይነት ልማታዊ ባለሃብት ከልማታዊ መንገድ እንዳይወጣ በልማታዊ መንገድ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሰራተኛ ድጋፍ ያስፈልጋል።ልማታዊ ባላሃብትና ሰራተኞች ከፍተኛ ተጠቃሚ ለማድረግና ዘለቂ እንዳስትሪ ሰላም ለማረጋገጥ ሁነኛ አቅጣጫ ስለሆነ ሰራተኞችና ልማታዊ ባለሃብቶች ሊከተሉት ይገባል።

በአንፃሩ ለኪራይ ሰብሳቢ ባለሃብት ሰራተኛው ጠንክሮ መፋለም አለበት።ኪራይ ሰብሳቢ ባለሃብት እንደማንኛውም ኪራይ ሰብሳቢ ጨለማን ይወዳል።ጨለማን ለመጠቀም ሲል ደግሞ በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር ይፈልጋል።ወደ ቀኝ አክራሪ ሃይል በፍጥነት የሚሳባሰበው ይህንን ሃይል ነው።የሰራተኛው ዲሞክራስያዊ መብት

እንዲታፈኑ የሚንቀሳቀሰው ይህኛው ሃይል ነው።ሰራተኞች እነኝህ ኪራይ ሰብሳቢ ባለሃብቶች አምርሮ መኮነን ብሎም መታገል ይገባል።በሰራተኛው ትግልና ጥንካሬ ወደ ልማታዊ ባላሃብ እንዲሳቡ ማድረግ ይቻላልም ይገባልም።

## 5.4.ኢህአዴግ፤ ሰራተኛው ከጎኑ ለማሰፍ መንቀሳቀስ ይገባል።

ኢ.ህአዴግ ሕብረተሰባዊ መሰረቱ አርሶአደር/አርብቶ አደር፣ሰራተኞች፣ የከተማ ነዋሪና አብዮታዊ ሙሁር መሆኑን ተደጋግሞ ተገልፀዋል።መዋቅራዊ ለውጥ ሲመጣ ይህንን የኢ.ህአዴግ መሰረት የሆነውን አርሶአደር በቁጥር እየቀነሰ የሚሄድበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀሬ ነው።በተግባርም እየታየ ያለው ይህንን ነው።ኢ.ህአዴግ ራሱን ወደገዢ መደብ ካልቀየረ በስተቀር ዋናው ህብረተሰባዊ መሰረቱ የሆነው አርሶአደር ወደ ባለሃብትና ሰራተኞች እንዲሁም ዝቅተኛና መካከልኛ ኑሮ ያለው የከተማ ነዋሪነት ሲቀየር ኢህአዴግ ህብረተሰባዊ መሰረቱ ይቀይራል።በዚህ ግዜ ህብረተሰባዊ መሰረቱ የሚሆኖው በአብዛኛው ሰራተኛ ቀጥሎ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች መሆናቸው የማይቀር ጉዳይ ነው።ስለዚህ ዋናው መዋቀራዊ ለውጥ እንዲመጣ እየሰራ ቀጣዩ የህበረተሰባዊ መሰረት ለሚሆነው ሰራተኛ መደብ መጠናከር መስራት ይገባል።

ከላይ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ ሰራተኛ በብዛት በአባልነት የኢ.ህኣዴግ አባል ድርጅቶች /ህወሓት፣ ብአዴን፣ኦህይድ ፣ ደኢ.ህዴን/መመልመል አለበት።ኢ.ህአዴግ በሚያካሄዳቸው የአመራር ስልጠናዎች በስፋት እንዲሰለጥኑ በተግባር እንዲፈተኑ ብቁ መሆናቸው የተረጋገጠ የሰራተኛ አመራሮች በተለያዩ የድርጅቱ የስልጣን እርከኖች እየተመደቡ እንዲሰሩ ማድረግ አለበት።


ታጁ ሙሓመድያሲን

muhamedyassintaju@gmail.com


09/08/2010ዓ/ም

**ዋቢ መፃሕፍት፡-**


- ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ!የኢ.ህአፓ ትራጀዲ፣1979ዓ/ም
- ምስረታ ሃገር ለኸ ፓርቲ ኣብ ኢትዮጵያ፣1979 ዓ/ም
- የኢንዳስትሪ ፖሊሲና ስትራቴጂ፣1994 ዓ/ም
- ሂወት ተፈራ፣ማማ በሰማይ፣2007ዓ/ም
- The International Labour Organization’s Fundamental Conventions, 2003
- እንዲሁም የተላያዩ የቡዙሃን መገናኛ